June 24, 2008

# መወደድን መውደድ ይወልደዋል !

## በቶሮንቶ የኢሕአፓ ሕዝባዊ ስብሰባ ሪፖርት፤

ከትናንት በስቲያ፥ ጁን 22 ቀን 2008 ዓ.ም የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች በቶሮንቶ የጠሩት ሕዝባዊ ስብሰባ ደማቅ በሆነ ሁኔታ ተካሄደ።



ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ በአስደንጋጭ ሁኔታ ወደ ውጭ ሀገሮች ከጎረፉትና በየደረሱባቸው ሀገሮች ትኩረታቸውን ወደ ሀገራቸው አዙረው ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ችግር መፍትሄ ፍለጋ ሰፊ አስተዋፅኦ ካደረጉት ኢትዮጵያዊያን መካከል፥ በካናዳ ሀገር በተለይም ቶሮንቶ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ወገኖች ጉልህ ቦታ አላቸው። ወደ ምዕራብ አገሮች የብዙሃኑ ስደት ከጀመረበት 80ዎቹ መግቢያ ጀምሮ፥ ቶሮንቶ ላይ ተቀማጭ የሆኑ አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያዊያን፥ ለኑሯቸው ወጭና ገቢ ሳያስቡ በቀጥታ ኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄድ ለነበረው ሁለገብ ትግል ተሳታፊዎች ሆነዋል። በዚህም በቀጣዩ ትውልድ ሲታወስ የሚኖር አኩሪ ታሪክ አስረካቢ ሚናቸውን ተወጥተዋል።

ኢሕአፓ እንደ ቀዳማይ የፖለቲካ ድርጅትነቱ በተጉዋዠ ትውልድ ስነልቦና ላይ የሰፈረ በመሆኑ፥ ስደተኞች በደረሱበት አካባቢ ሁሉ አብሮ ይደርሳል። ስለሆነም በአዲሱ የካናዳ ኢትዮጵያዊያን ማህበረሰብ ውስጥ ገና ከጅምሩ እያያቆጠቆጡ የመጡትን ነፃ የብዙሃን

መገናኛ ውጤቶች - እንደ ሐዋርያ የመሳሰሉት- እንዲወለዱና እንዲዳብሩ እያበረታታና እያሳተፈ፥ ማህበረሰቡ የገነባቸውን የብዙሃን ድርጅቶች - እንደ ኢቲዮ-ካናዳዊያን የሰላምና ዕድገት ድርጅት በቶሮንቶ (ኢፒዶት) የመሳሰሉትን - እየደገፈና ሚናቸውን እንዲወጡ መርህአዊ ምርኩዝ እየሆነ የትግል ችቦውን በማቀጣጠል፥ አዲሱ ማህበረሰብ መልካም ህልም አልሞ ብሩህ ዓለም እንዲናፍቅ ተስፋ ሆኖት መቆየቱ እውነት ሆነ።

እንደሚታወሰው፥ ቀደም ሲል ከብዙሃኑ የስደት ጉዞ በፊት፥ በኢሕአፓ ውስጥ ተጸንሶ የተወለደው የአንጃና ብተና አደጋ፥ ፓርቲውን በውስጥም በውጭም ክፉኛ አዳክሞት ነበር። እንደሌሎቹ አካባቢዎች ሁሉ ድርጅቱ በቶሮንቶ እንቅስቃሴውን መልሶ መቀጠል የ ቻለውና ትግሉን በቀጥታ ከአገርቤቱ ጋር ያያያዘውም በዚሁ በ80ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት ውስጥ እንደነበር ይታወሳል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው የሚኖሩ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎቹ፥ በአንድ በኩል በአንጃ ክስተትና በብተና ሴራ የተጎዳውን ድርጅታቸውን መልሰው እየገነቡ፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ሲካሄድ ለቆየውና ለቀጠለው ሁለገብ ህገራዊ ትግል የበኩላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን ቀጠሉ።

ዛሬም እንደገና፥ ኢሕአፓ ራሱን መልሶ ካደራጀ ከ25 መራራ የትግል ዓመታት በሁዋላ ያለፈው ተመሳሳይ ሁኔታ ጣጣ ፈንታ-እጣ ተፈጥሮበት፥ በውስጠ ፓርቲ ትግል ተበጥሮ፥ በአንጃ አደጋ ተፈትኖ በመውጣት የሕዝባዊው ትግል ፋኖነቱን እያረጋገጠ ባለበት ወቅት ላይ ነው በቶሮንቶ አባላቱና ደጋፊዎቹ በልበ ሙሉነት ከወገኖቻቸው ጋር ለመነጋገር ሕዝባዊ ስብሰባ የጠሩት። "ጋን ቢለቀለቅ ማድጋ ይሞላል" እንዲሉ፥ ከውስጥም ከውጭም ያለማቋረጥ በሚወረወር ጦር የሚወጋው ኢሕአፓ፥ ዛሬም "አለንልህ አለሁ በለን" የሚል የሕዝብ ወገን ድጋፉንና ተስፋውን አልነፈገውም። እናም፥ ጁን 22፥ 2008 በተጠራው የቶሮንቶው የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ስብሰባ ቁጥሩ እንደወትሮው የበረከተና ለህገሩ ጉዳይ ስሜቱ የጋለ የሕዝብ ወገን ታድሞበት ውሏል።

በዕለቱ ለተካሄደው ስብሰባ ፓርቲውን በኦፊሴል ወክለው የትገኙት፥ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ አባል የሆኑትና በኢሕአፓ የትግል ታሪክ ውስጥ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ፀንተው በመቀጠል ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ የሚገኙት አቶ ተገኝ ሞገስ ናቸው። አቶ ተገኝ ስለህገራችን ጉዳይ ከኢሕአፓ ለመስማት በጉጉት በአደራሹ ለታደመው ሕዝብ ሥርዓትና ትህትና በተሞላበት መንፈስ የእንኳን ደህና ቆያችሁ ሰላምታቸውን ከተለዋወጡ በሁዋላ በቀጥታ ወደመጡበት ርዕሰ ጉዳይ በመግባት 'የህገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ምን ይመስላል፥ ትግሉ የት ላይ ደርሷል፤ ኢሕአፓስ ምን እየሠራ ነው?" በሚለው ላይ አጠቃላይና መሪ የሆነ ገለጻ አደረጉ። ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ጭንቅ ላይ መሆናቸውን፥ ሕዝባችን በረሃብ ጠኔ መጠውለጉን፥ ህገሪቱ ዳር ደንበሯ መደፈሩን፥ - በአጠቃላይ ኢትዮጵያና ሕዝቧ በህገር በቀልና የወራሪነት ጠባይ ባለው የወያኔ አገዛዝ መዋረዳቸውን ስሜትን በሚርድ አንደበት መልእክታቸውን አስተላለፉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሉ ከብዶት፥ ጥቃቱ በዝቶበት፥ ረሃብና ጥሙ ጠንቶበት ሊችለውና ሊሸከመው ከማይችለው ደረጃ መድረሱን የገለጡት አቶ ተገኝ ሞገስ፥ ኢሕአፓ ዛሬም እንደትናንቱ በትግሉ አውድማ ላይ በግንባር ተሰልፎ የሚቻለውን ሁሉ በማከናወን ላይ እንዳለ ፈርጠም ብለው ተናግረዋል። ሱዳን የደፈረው የህገራችን ዳር ድንበር በኢትዮጵያ ሕዝብ ተጋድሎ መከበር እንዳለበት ገልጸው፥ በተናጠልና ለቡድናዊ ጥቅም ሲባል ውር ውር የሚባለውን ሩጫ ብኩንነት ከማስገንዘባቸውም በላይ፥ የደንበሩ ችግር ለአካባቢው ተወላጆች ብቻ መተው የሌለበት ህገራዊ አደራ መሆኑንም አስምረው ተናግረዋል።



**የክብር እንግዳው ንግግራቸውን እንደጨረሱ ቀሪው ክፍለ ጊዜ ከቤቱ ተጨማሪ አስተታየት መለዋወጫ፥ የጥያቄና መልስ ሆኖ ሰፊ ጊዜ ሸፈነ፡፡ በስብሰባው ላይ ከነበሩት አዛውንቶች መካከል ኢሕአፓዎች እናታችን ወይም 'ማዘር' የሚሏቸው እናት አሰለፈች ነበሩ፡፡ እናት አሰለፈች በረጅሙ ትግል ውስጥ በጉልህ የሚታወቁና ከፍተኛ ክብርን ያተረፉ ታጋይ እናት ሲሆኑ፥ ከአንበሳ አውቶቡስ የሠራተኛ ማህበር በኩል ኢሕፓን የተቀላቀሉት በ**1967 **ዓ.ም (እንደ አገራችን አቆጣጠር) እንደሆነና ኢሕአፓ ላካሄደው የትጥቅ ትግልም በሜዳ ለመሳተፍ አስራአንድ የሚሞቁና የሚናፍቁ ልጆቻቸውን ትተው እንደተቀላቀሉ የትግል ታሪካቸው ንባቤ ይተርካል፡፡**



ከክብር እንግዳው ከአቶ ተገኝ ሞገስ ንግግር ለጥቆና በሁዋላም ከቤቱ በተነሱ ነጥቦች ላይ እናት አሰለፈች ባስደመጡት ንግግር የተሳታፊውን ሕዝብ ሙሉ ቀልብ ከመሳባቸውና ስሜቱን ከመቀስቀሳቸው ባሻገር የስብሰባውን ሂደትና አፈጻጸም ግልጽ አቅጣጫ ማስያዛቸው ተስተውሏል፡፡ ተሰብሳቢው ሕዝብ ንቅንቅ ብሎ በመቆም በደማቅ ጭብጨባ አክብሮቱን የገለጸላቸው እኒህ እናት፥ በስብሰባው ላይ ተገኝተው የስብሰባውን መንፈስ ሊያውኩ የሞከሩትን የድርጅቱ አንጃዎች በርትዑ አንደበት በመገሰጽ በተግባራቸው እንዲያፍሩና እንዲጸጸቱ እድል ሰጥተዋቸዋል፡፡

ከቤቱ የተነሱት ገንቢ አስተያየቶችና ጥያቄዎች እንዳሉ ሆኖ፥ በቅርቡ በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረው አንጃ አባላት ያነሷቸው ጥያቀዎች አስተዛዛቢ ከመሆናቸው በላይ በራሳቸው

ላይ የባረቀ አዳፍኔ ነበር። በሥርዓት እጃቸውን ለጥያቄ አውጥተው ባገኙት መድረክ ላይ ከስብሰባው መንፈስ ውጭ የሆነና የቂም ቁርሾ ያጠላበት ጥያቄ በማቅረባቸው ተሰብሳቢው ሕዝብ በከፍተኛ ድምጽ አይናችሁን ላፈር ብሎ አሳርፏቸዋል። የአንጃው አባላት ጥያቄዎች ግለሰባዊ የሆኑና ድርጅቱ ውስጥ በነበሩበት ወቅት ተፈጸመ የሚሉትን ፈጠራ ይጠቅመናል ብለው በአደባባይ "ለማጋለጥ" ያደረጉትን ከንቱ ሙከራ ተሰብሳቢው ሕዝብ በአዘኔታ ከመንቀፉ በላይ፥ ተጠርቶ የመጣበትን ጉዳይ ግልጽ በማድረግ 'የሕዝባችን እሮሮና የሀገራችን ችግር ተረድተን የምንችለውን ለማድረግ ነው የመጣነው፤ ከድርጅቱ ጋር ላላችሁ እሰጥ አገባ አይመለከተንም፤ ሌላ ጊዜ ሌላ ቦታ አድርጉት" በሚል ሃይለ ቃል ነበር ከዳር እስከ ዳር ያስተጋባው። በተሳካ ሁኔታ ስብሰባው ካበቃ በሁዋላ አንዳንድ ተቆርቋሪዎች ለስብሰባው አዘጋጆች በሃዘኔታ እንዳስታወሱት "እነዚህ ከድርጅቱ የተለዩ ወገኖች በአደባባይ የሚያቀርቡት ጥያቄ እውነት ከሆነ እኮ በቀጥታ ለጠላት ነው እያጋለጧችሁ ያለው፥ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ እየጠቀሙና መረጃ እየሰጡ ያለው እኮ በቀጥታ ለጠላት ነው" ሲሉ የተሰማቸውን ሃዘኔታ ገልጸዋል።




ከዚህ ስኬታማና የተሚላ ስብሰባ በሁዋላም፥ በቶሮንቶ ከተማ ውስጥ እውቅ በሆነው የላሊበላ ምግብ ቤት የራት ምሽት የተደረገ ሲሆን በሥነ ሥርዓቱ ላይ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ተጋባዥ ተገኝቷል። በእራት ግብዣው ላይ የተገናኙት ወገኖች ሁኔታው በጣም ስላስደሰታቸው እስከ ንጋቱ 2 ኤ.ኤም ድረስ በሞቀ ውይይትና መዝ ናናት መልካም ጊዜ አሳልፈዋል። እለቱ ቅንጅት በኢንጅነር ሃይሉ ሻዎል መሪነት አዲስ አበባ ላይ የተሳካ ጉባኤ እካሂዶ የተነሳበት አጋጣሚ በመሆኑና በቶሮንቶ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎችም በእራት ግብዣው ላይ ተገኝተው ስለነበር፥ የአካባቢው ኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች የአንኳን ደስ አላችሁ መልእክት ያስተላለፉላቸው ሲሆን፥ በስኬት የተጠናቀቀው ጉባኤ የአንድነት ሃይሉን ሞራል የሚገነባና ትግሉን ወደፊት የሚያራምድ መሆኑንም አውስተዋል።

በመጨረሻም፥ የክብር እንግዳው አቶ ተገኘ ሞገስ የመሰነባበቻ ንግግር በማድረግ፥ የስብሰባውን አዘጋጆችና ተባባሪዎቹን አመስግነዋል፤ ለቶሮንቶ የቅንጅት አባላትንና ደጋፊዎችም በስኬታሙ ጉባኤያቸው የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽና ላሳዩት የትግል ትብብርም በማመስገን ንግግራቸውን ቋጭተዋል።



22.6.2008

በዚህ አጋጣሚ ወደ ስብሰባው ለመጡ ድንቅዬ ወገኖችና እንዲሁም በተለያየ ሁኔታና ምክንያት ሳያዳርሳቸው ቀርቶ ላልመጡ ወገኖች፥ ነገር ግን ዘወትር የኢሕአፓን እንቅስቃሴ ያገባናል ብለው ለሚከታተሉና ለሚደግፉት ሁሉ፥ በቶሮንቶና አካባቢው የምንገኝ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች ላቅ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። ዛሬም እንደ ጥንቱ የማህበረሰባችንን ፍቅርና ድጋፍ ለማትረፍ፥ ድርጅታችን ኢሕአፓ ባወረሰን የትግል ሥነ-ሥርዓትና አይበገሬ ጽናት ታንጸን፥ አያሌ ሰማእታት ጀግኖች የተዋደቁለትን ሕዝባዊ ትግል ከግቡ ለማድረስ በቅንነትና በታማኝነት ለመቀጠል ቃል እንገባለን።

ቸር ይግጠመን!!
በቶሮንቶና አካባቢው የኢሕአፓ ድጋፍ ኮሚቴ